EARLY STAGES
STRONG BEGINNINGS • BRIGHT FUTURES



# ወላጆች እንደ ተሟጋቾች

የልዩ ትምህርት ምዘና እና የብቁነት ሂደት ግራ የሚያጋባ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ኧርሊ ስቴጅስ (Early Stages) እርስዎን ማለትም ወላጅ ልጅዎን እንዲረዱ ለማገዝ እዚህ ይገኛል።

## ተሟጋች ወይም ጠበቃ ምንድነው?

ጠበቃ ለሌሎች ይደግፋል፤ ይናገራል። ለልጅዎ ተሟጋች ወይም ጠበቃ እንደመሆንዎ መጠን ለትምህርት ፍላጎቶቻቸው አስፈላጊ ድምጽ ነዎት።

## የልጅዎ ምርጥ ጠበቃ ለመሆን ጠቃሚ ምክሮች

- መረጃ ያግኙ። በዚህ ሂደት ውስጥ ስለ ልጅ እድገት፣ የልዩ ትምህርት ሂደት እና መብቶችዎ መረጃ ማግኘት ለችግሮች ምላሽ እንዲሰጡ እና የልጅዎ ቡድን ጠንካራ አባል እንዲሆኑ ያግዝዎታል።
- አዎንታዊ አስተሳሰብ ይያዙ። ይህ አስተሳሰብ ገምጋሚዎችን፤ መምህራንን እና አገልግሎት ሰጪዎችን ጨምሮ ከልጅዎ ቡድን ጋር በደንብ እንዲሰሩ ይረዳዎታል።
- ስለ ልጅዎ ዕድገት ጉጉ (curious) ይሁኑ። በልጅዎ እድገት ላይ ፍላጎት እና ንቁ መሆን ስለ እድገታቸው እና የመማር እድገታቸው እንዲያውቁ ያደርግዎታል።
- ከልጅዎ ቡድን ጋር ይገናኙ። እርስዎ እና የልጅዎ ቡድን ሁላችሁም አብራችሁ ነው የምትሰሩት፣ እና ጥሩ የሐሳብ ልውውጥ ከቡድን ሥራው በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው።
- የድጋፍ አውታር (support network) ይፍጠሩ። በዚህ ሂደት ውስጥ መመሪያ እና ስሜታዊ ድጋፍ ሊሰጡዎት የሚችሉ የወላጆችን እና ሌሎች ባለሙያዎችን ያግኙ።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS



## የድጋፍ አውታር (Support Network) ምንድን ነው፤ እና ምን መካተት አለበት?

**ወደ ልዩ ትምህርት ሂደት ሲመጣ፣ የድጋፍ አውታር (support network) የሚያካትተው ልጅዎን በደንብ የሚያውቁ ሰዎችን እና፤**

- ከእርስዎ ጋር ወደስብሰባዎች የሚመጡ
- የሙያ እውቀት የሚያካፍሉ
- ድጋፍ የሚለግሱ እና መናገር በሚፈልጉ ጊዜ የሚያዳምጡ
- ልጅዎን እንዴት መርዳት እንደሚችሉ በመማር ሂደት የሚረዱዎት

የድጋፍ አውታር እርስዎ የሚፈልጉትን ማንኛውንም ሰው ያካትታል፤ ለምሳሌ፤

- የቤተሰብ አባላት ወይም የሚታመኑ ጓደኞች
- ሃይማኖታዊ እና መንፈሳዊ አማካሪዎች
- የህጻናት እንክብካቤ ሰጪዎች
- ዶክተሮች እና የጤና እንክብካቤ ሰጪዎች
- ልጅዎን በደንብ የሚያውቅ የት/ቤት አባል

## አድቮኬሲ (Advocacy) ምን ይመስላል?

**አድቮኬሲ (Advocacy) የሚከተሉትን ሊመስል ይችላል፤**

- የልጅዎን ጥንካሬ እና ፍላጎቶች ማወቅ
- የሚያስጨንቁዎትን እና ጥያቄዎችን ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ማሳወቅ
- ልጅዎ እንዴት እንደሚማር፣ እንደሚጫወት እና እንደሚያዳብር አስተያየቶችን መጻፍ
- ከአውታረ መረብዎ ድጋፍ መጠየቅ
- በሚፈልጉበት ጊዜ የትርጉም እና የትርጓኔ አገልግሎቶችን መጠየቅ



**እርስዎ በልጅዎ ሁኔታ ላይ ባለሙያ (expert) መሆንዎን ያስታውሱ።**
**እርስዎ የልጅዎ ምርጥ ጠበቃ ነዎት።**

(202) 698-8037 | info@earlystagesdc.org | www.earlystagesdc.org